# አልታየን አለ

ትውልድ እያለፈ ፣ ትውልድ እየተካን
አንድ ቀን ሳይደላን ፣ ሁሌ እንደተገፋን
ታሽን ተወቀጥን ፣ እንደ ቁርበት ፣ ለፋን
አቃለሉ ጣሉን ፣ ተናቅን ፣ ተተፋን
የደላን ይመስል ፣ ቅንጣትም አልከፋን
በየፊና መሮጥ ፣ ከምድር እስኪያጠፋን
መባነን አልቻልንም ፣ ጥንብ እየከረፋን ።

አሰሩ አሰቃዩ ፣ ገደሉ መተሩን
ታሪክን አጠፉ ፣ አቃጠሉ ደብሩን
ከትውልድ ስፍራችን ፣ ነቅለው አባርሩን
ሸጡት ሸነሸኑት ፣ በሃራጅ አገሩን
ለዘራፊ ሰጡን ፣ ከፋፈቱት በሩን
ስንቴ እንሞታለን ፣ ከነነፍስ ሲቀብሩን ።

ከንሰሳት ካራዊት ፣ አነስን አልተሻልን
ካገር ተባረርን ፣ ከርስት ተነቀልን
ቤቱን በላያችን ፣ናዱ አፈረሱልን
ለህንድና ለአረብ ፣ አገሩን ሸጡልን
ጠምደው አረሱብን ፣ በግፍ ተሰቀልን
ጀግንነት የት ገባ ፣ ብዙ የተባለልን
ምነው እናታችን ፣ ወንድ አትወልድልን ?

የአረብ የቻይና ፣ ምስለኔ ቅጥረኛ
ባንዳ ፣ የባንዳ ልጅ ፣ የሞት መላክተኛ
አገሩን በካዳ ፣ ልበ ሙቅ ፣ ምንደኛ
ኢትዮጵያ ስላልን ፣ ሆነን ወንጀለኛ
በጠላት ተቀጥሮ ፣ ሲያረገን እስረኛ
ምነው መሸቶ ቀረ ፣ አልነጋ አለ ለኛ
መቆጨት ተስኖን ፣ ተጠቃን ከፉኛ ።

የመከራው ብዛት ፣ አላባራ እያለ
ጫንቃው ካልከበደው ፣ እየተበደለ
በዘር በሃይማኖት ፣ ከተከፋፈለ
አለሁ አይባልም ፣ በቁም ሞቶ ሳለ ።
ዛሬስ አሻፈረኝ ፣ ማለት ካልተቻለ
በህብረት ተነስተን ፣ ትግል ካልቀጠለ
ትላንት ተመስግኖ ፣ ነገ ይብስ የለ
ምን አዚም ፣ ጋረደን ፣ አልታየን አለ ?።

ታዛቢው ... March 11, 2012